# አስፈሪዉ ሙስና ከፊታችን ነዉ!!!!

አብይ ጨልቀባ[1] 05/17/13

***መግብያ***

ለዚህ ፅሑፍ መነሻ ሃሳብ የሆነኝ በቅርቡ የከፍተኛ የመንግስት ባለስልጣናት በሙስና ወንጀል ተጠርጥረዉ በህግ ቁጥጥር ዉለዋል የሚል ዜና ነዉ፡፡ በሚኒስትርነት ማዕርግ የኢትዩጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለ ስልጣን አቶ መላኩ ፈንታ፣ ምክትላቸዉ አቶ ገብረዋህድ ወልደጌርግስ፣ እንዲሁም በርከት ያሉ ከፍተኛ ባለስልጣናት እና ታዋቂ ባለ ሃብቶች በሕግ ቁጥጥር ዉለዋል፡፡ የዚህ ፅሑፍ አላማ የሙስና ማንነትን እንደመነሻ ሃሳብ አድርጎ የሙስና የምንዋጋባቸዉ ስልቶች በማስቀመጥ አስፈሪዉ ሙስና ከፊታችን እንደሆነ የሚደመድም ነዉ፡፡

**ሙስና አስተሳበብ እንጂ ድርጊት አይደለም!**

ለመሆኑ ሙስና ምንድን ነዉ? በዚህ አጭር መጣጥፍ የፀሓፊዉ እምነት ሙስና አስተሳሰብ እንጂ ድርጊት አይደለም፡፡ በሌላ አነጋገር ሙስና ብልሹ አስተሳሰብ ነዉ፡፡ ድርጊት የብልሹ አስተሳሰብ የመጨረሻ ምርት ነዉ፡፡ ድርጊት በብዙ ነገሮች ሊገለፅ ይችላል፡፡ ለምሳሌ በስልጣን መባለግ፣ ለሶስተኛ ወገን ያላግባብ ጥቅም መስጠት፣ ያላግባብ መበልፀግ ወ.ዘ.ተ የመሳሰሉትን ሊያካትት ይችላል፡፡ ሙስናን ለማስወገድ ድርጊቱን በማስወገድ ሙስናን መዋጋት አይቻልም፡፡ ሙስናን ለማስወገድ ሙሰኞችን ማስወገድ ተመራጭ መፍትሄ ሊሆን አይችልም፡፡ ሙሰኞችን በህግ ቁጥጥር ሥር ማዋል የመፍትሄዉ ትንሹ አካል ነዉ፡፡ ለዚህ አስተሳሰብ ሊደግፍ የሚችል አንድ ጉዳይ ላንሳ፡፡ ስለ ድህነትን ጉዳይ፡፡ ድህነት በሁለት መንገድ ማስወገድ ይቻላል፡፡ አንደኛዉ የድህነት ምንጭ የሆነዉን ምክንያት ማድረቅ ነዉ፡፡ ሁለተኛዉ ድሆችን ማስወገድ ነዉ፡፡ የመጀመርያዉ ተመራጭ መፍትሄ ሲሆን ሁለተኛዉ ግን መፍትሄ እንካ እየሆነ አማራጭ ግን ሊሆን አይችልም፡፡

በተመሳሳይ መልኩ ሙስናን በሁለት መንገድ መዋጋት ይቻላል፡፡ አንደኛዉ የሙስና ምንጭ የሆነዉ ብልሹ አስተሳሰብ መዋጋት ነዉ፡፡ ይሄ ማለት ብልሹ አስተሳሰብ በጤናማ አስተሳሰብ መቀየር ማለት ነዉ፡፡ አንድ አስተሳሰብ መዋጋት የሚቻለዉ በሌላ አስተሳሰብ በመተካት ብቻ ነዉ፡፡ በኢትዩጵያ ከሙስና ጋር በተያያዘ የብልሹ አስተሳሰብ ምንጭ ደግሞ የፓለቲካ ባህል ነዉ፡፡ ስለሆነም የሙስና ምንጭ ዙሮ ዙሮ የፓለቲካ ባህል ነዉ፡፡ ምክንያቱም በኢትዩጵያ ሙስና ለብዙ አመታት ባህል ሁኖ ቆይታል፡፡ ባህል የአንድ ስርአት እና ትዉልድ ዉጤት አይደለም፡፡ የብዙ ስርአቶች እና ትዉልዶች ድምር እንጂ፡፡ አንድ ስርአት እና ትዉልድ ለብቻዉ ባህል የመፍጠር አቅም በጣም ዉሱን ነዉ፡፡ ባህል ለመቀየር

[1] አቶ አብይ ጨልቀባ በአምቦ ዩኒቨርስቲ መምህር ናቸዉ፡፡ በኢሜይል አድራሻቸዉ chewabiy@gmail.com ማግኘት ይቻላል፡፡

የስርአቶች እና ትዉልዶች የጊዜ ኢንቨስትመንት ይጠይቃል፡፡ የሙስና ባህል እጣ ፈንታ ከዚሁ የተለየ አይደለም፡፡ ስለሆነም የሙስና ባህል በሌላ ጥሩ ባህል መቀየርን ይጠይቃል፡፡ ይህ እንደተጠበቀ ሁኖ ሁለተኛዉ መፍትሄ ሙሰኞችን ማስወገድ ነዉ፡፡ ሁለተኛዉ መፍትሄ ጠቀሜታዉ ትንሽ ነዉ፡፡ ምክንያቱም ሙሰኞችን አይደለም ሙስናን የፈጠሩት፡፡ ሙስና ነዉ ሙሰኞችን የፈጠረዉ፡፡ ስለሆነም ድርጊት አይደለም ሙስና የፈጠረዉ፡፡ አስተሳሰብ ነዉ ሙስናን የፈጠረዉ፡፡ ሙስና የተቀዳበት ምንጭ ደግሞ ብልሹ የሆነ አስተሳሰብ ነዉ፡፡ ስለሆነም የመጨረሻ የመፍትሄ አካል ምንጭን ማድረቅ ነዉ፡፡

**"የመንግስት ሌቦችን" ማሰር የመፍትሄዉ ትንሹ አካል ነዉ!**

"የመንግስት ሌቦችን" ማሰር የመፍትሄዉ ትንሹ አካል ነዉ የምልበት ምክንያት የመንግስት ሌቦች በፀረ ሙስና ሲስተም ያላቸዉ ሚና አናሳ ስለሆነ ነዉ፡፡ ለመሆኑ ሲስተም ምንድን ነዉ? ሲስተም እንደ አንድ መቅደስ ማየት ይቻላል፡፡ መቅደስ መሰረት፣ ምሰሶዎች እንዲሁም ጣራ ነዉ ያለዉ፡፡ መቅደስ መሰረቱ የሕብረተሰብ እሴቶች እና የሕዝብ ንቃት ወይም ግንዛቤ ሊወክሉ ይችላሉ፡፡ ስለሆነም ወደ ሙስና ጉዳዮች ስናመጣዉ የመቅደሱ መሰረት ሙስና የሚፀየፍ ሕብረተሰብ መሆን አለበት፡፡ የመቅደሱ ምሰሶዎች ደግሞ ሕግ አዉጪ፣ ሕግ አስፈፃሚ፣ ፍርድ ቤት፣ ሙስናን የሚታገል ተቋም፣ሲቪል ማህበረሰብ፣ ሚድያ፣ ነፃና እና ፍትሃዊ ምርጫ፣ የፓለቲካ ቁርጠኝነት ፣ የዳኝነት ነፃነት እና የመሳሰሉት ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ የመቅደሱ ጣራ ለልማት፣ የሕግ ልእልና እንዲሁም ጥራት ያለዉ ኑሮ ሊወክል ይችላል፡፡ የኢትዮጵያ የፀረ-ሙስና ትንቅንቅ ችግሩ የሲስተሙ መሰረት የተገነባዉ በአሸዋ ላይ ስለ ሆነ ነዉ፡፡ በአሸዋ የተገነባ መቅደስ መፍረሱ አይቀርም፡፡ ስለሆነም በኢትዮጵያ የፀረ-ሙስና ትንቅንቅ መሰረት የተገነባዉ ሙስና እንደ አንድ የፓለቲካ ባህል አድርጎ የሚቆጥር ማሕበረሰብ ዉስጥ ስለ ሆነ ነዉ፡፡ መሰረቱ ከሌለ የፓለቲካ ቁርጠኝነት ቢኖርም ባይኖርም፣ የዳኝነት ነፃነት ቢኖርም ባይኖርም፣ ስልጣን የያዘዉ ፓለቲካ ፓርቲ ቢቀየርም ባይቀየርም የፀረ-ሙስና ሲስተሙ በተገቢ ሁኔታ አይሰራም፡፡ ምሰሶዎች የቆሙበት መሰረት ሊፈርስ የሚችል መቅደስ ስለ ሆነ፡፡ "የመንግስት ሌቦች" በሕግ ፊት ማቅረብ የመቅደሱ አንድ ምሰሶ የሚወክል ነዉ፡፡ "የመንግስት ሌቦችን" በሕግ ፊት ማቅረብ የሚያመላክተዉ የመቅደሱ ምሰሶዎች እንደ ፍርድ ቤት እንዲሁም ሙስና የሚዋጉ ተቃሞች በትክክል እየሰሩ መሆኑ አመላካች ነዉ፡፡ ከዚህ የዘለለ ግን ትርጉም የለዉም፡፡ምክንያቱም ምሰሶ ከምሰሶዉመቱ ሊዘል አይችልም፡፡ ምሰሶ መሰረት ሊሆን አይችልም፡፡ ምሰሶዉ የተገነባዉ ሊፈርስ በሚችል መሰረት ነዉ፡፡ ስለሆነም "የመንግስት ሌቦችን" ማሰር የመፍትሄዉ ትንሹ አካል ነዉ፡፡

**የእስሩ አንድምታዎች**

የከፍተኛ ባለ ስልጣናት መታሰር ያለዉ ትርጉም አንድ እና አንድ ነዉ፡፡ እሱም በኢትዩጵያ ሙስና ለመዋጋት ለወደፊቱ በሚደረገዉ ትግል ሲስተም ከአስተሳሰብ ቀጥሎ ለመጀመርያ ጊዜ ተኪ የሌለዉ ብቸኛዉ መሳርያ መሆኑ የሚያሳይ ነዉ፡፡

በቀድሞ ጠቅላይ ሚኒስተር አቶ መለስ ዜናዊ የሚመራዉ የነበረ የኢህአዴግ መንግስት እና አሁን በስልጣን ላይ ያሉት አቶ ኃይለማርያም ደሳለኝ ሙስና ለመዋጋት እየተከተሉት ያሉት ስትራቴጅ በአብዛኛዉ ተመሳሳይ ነዉ፡፡ ሙስና በዋናነት በአስተሳሰብ ነዉ መዋጋት የሚል እምነት ነዉ፡፡ ስለሆነም የትናንት ኢህደአዴግ እና የዛሬ ኢህአዴግ አንድ ናቸዉ፡፡ በአንድ ነገር ግን ይለያያሉ፡፡ የቀድሞ ጠቅላይ ሚኒስተር አቶ መለስ ዜናዊ አስተዳደር ሙስናን ለመዋጋት ከአስተሳስብ እና ከህግ ጉዳይ ጎን ለጎን የአቶ መለስ ዜናዊ ስብእና ራሱን የቻለ አንድ አጋዥ መሳርያ ነበር፡፡ የቀድሞ ጠቅላይ ሚኒስተር አቶ መለስ ዜናዊ በህዝብ ዘንድ የነበራቸዉ ተቀባይነት (legitimacy and/or popularity ) ራሱን የቻለ ስርአትን ጎን ለጎን ሊተካ የሚችል ሌላ “ስርአት” ነበር፡፡ የቀድሞ ጠቅላይ ሚኒስተር አቶ መለስ ዜናዊ በፓርላማ ቀርበዉ ስለ ሙስና በሚናገሩበት ወቅት በህዝብ ዘንድ ተቀባይነታቸዉ ከፍተኛ ነበር፡፡ በዚህ ፀሓፊ እምነት ጠቅላይ ሚኒስተር አቶ መለስ ዜናዊ ከሙስና ጋር በተያያዘ ትተዉት የሄዱት አንድ የማይተካ ሌጋሲ አለ፡፡ ካላቸዉ ትልቅ ስብእና የተነሳ እና በሌሎች የመንግስት ባለስልጣናት የነበራቸዉ ተሰሚነት አንፃር ሙስና ሊያስቀጣ ይችላል የሚል ስነ ልቦናዊ ጫና መጫን የሚችሉ ብቸኛዉ ግለ ሰብ ነበሩ፡፡ ይህ ፅሑፍ በምፅፍበት ወቅት በሌሎች ከፍተኛ ባለ ስልጣናት የስነ ልቦናዊ ጫና ማሳደር የሚችል ግለ ሰብ በኢህአዴግ በአሁኑ ወቅት የለም፡፡ ለቀጣይ የሚታይ ቢሆንም፡፡

የአሁኑ ጠቅላይ ሚኒስተር አቶ ኃይለማርያም ደሳለኝ አስተዳደር ግን ሶስተኛዉ ማሳርያ በእጁ የለም፡፡ ሙስናን በሁለት መሳርያ ብቻ ነዉ መዋጋት የሚችለዉ፡፡ በአስተሳሰብ እና በህግ ጉዳይ ብቻ፡፡ ስለሆነም የአሁኑ ጠቅላይ ሚኒስተር አቶ ኃይለማርያም ደሳለኝ አስተዳደር የሙስና ጉዳዮች በሙስና የተጠረጠሩት ከፍተኛ ባለስልጣናት በህግ ፊት አቅርቦ ከመከራከር እና ማስፈረድ ሌላ አማራጭ የለዉም፡፡ የጠቅላይ ሚኒስተር አቶ ኃይለማርያም ደሳለኝ አስተዳደር በሌሎች ባለስልጣናት የስነ ልቦናዊ ጫና ማሳደር እንደ ግለሰብ የማሳደር አቅሙ የለዉም፡፡ ቀጣይ የሚታይ ቢሆነም፡፡ የስነ ልቦናዊ ጫና ማሳደር የሚቻለዉ በሙስና የተጠረጠሩ ባለስልጣናት በህግ ቁጥጥር ስር በማስገባት ብቻ ነዉ፡፡ ስለሆነም በቀድሞ ጠቅላይ ሚኒስተር አቶ መለስ ዜናዊ እና አቶ ኃይለማርያም ደሳለኝ የሚመራዉ ኢህአዴግ ያለዉ ልዩነት የስነ ልቦናዊ ጫና ማሳደር ችሎታ ብቻ ነዉ፡፡ በኢትዩጵያ በሙስና በሚደረገዉ ትንቅንቅ የስነ ልቦናዊ ጫና በባለ ስልጣናት ማሳደር ራሱ የቻለ ስርአትን ሊተካ የሚችል ሌላ ስርአት ነዉ፡፡ “የስነ ልቦናዊ ጫና ስርአት” በግለሰቦች

ስብእና እና ተሰሚነት የሚመረኮዝ ነዉ። ስለሆነም እንድምታዉ አንድ እና  አንድ ነዉ። ኢትዮጵያ ከአሁን ብሃላ ሙስና የምትታገለዉ የተጠናከረ ስርአት( ህግ እና ህግ መሰረት ያደረገ) በመመስረት መሆኑ ብቻ ነዉ። ይሄ ስርአትም እየተዘረጋ እና እየተጠናከረ መምጣቱን አንድ ምልክት ነዉ፤ በቅርብ የተደረገዉ እስር።

**አስፈሪዉ ሙስና ከፊታችን ነዉ!**

አባይን ያላየ በምንጩ ይደነቃል ይላል ያገሬ ሰዉ። የቅርብ "የመንግስት ሌቦች" በሕግ ቁጥጥር መዋላቸዉ ምንጭ እንጂ ራሱ አባይ ሊሆን አይችልም።  ምክንያቱም በሙስና እና ሙሰኞች ያለዉ ትስስር አስፈሪ ገፅታዉ የሚወጣዉ በቀጣይ አስር እና ሃያ አመታት ነዉ። ለዚህ ምክንያት የሆነኝ በሙስና እና በሙሰኞች እንዲሁም የኢኮኖሚ እድገት ያለዉ ትስስር ለዚህ ጉዳይ ማሳያ ሊሆን ይችላል። በኢኮኖሚክስ ዲሲፕሊን የ U inverted መላምት የሚባል አስተሳሰብ አለ።  U የእንግሊዝኛ ቃል የሚወክል ሲሆን ሲገለበጥ የአማርኛዉ የ በ ቅርፅ ይይዛል። የ U inverted ማለት የአማርኛዉ ፊደል በ ማለት ነዉ። የአማርኛዉ ፊደል በ በሁለት ምሰሶዎች የቆመ ሲሆን የፊደሉ የላይኛዉ ክፍል የተንጣለለ ሜዳ ወይም ረዥም ድልድይ አድርገን መዉሰድ ይቻላል።

የዚህ አስተሳሰብ ተግባራዊነቱ በኢኮኖሚ እድገት እና በገቢ አለመመጣጠን ያለዉ ዝምድና የሚያሳይ ሲሆን በኢኮኖሚ በማደግ ላይ ያሉ አገሮች በዜጎች የሚታየዉ የገቢ አለመመጣጠን የእድገቱ የመጀመርያ ወቅቶች (አስር አመት ሊሆን ይችላል) በከፍተኛ መጠን እየጨመረ ይሄዳል።  ከዚህ ቡኃላ የእድገቱ ከአስር አመት እድሜ ሲበልጥ በዜጎች የሚታየዉ የገቢ አለመመጣጠን የኮንስታንት ባህሪ ይይዛል። ይሄን የአማርኛዉ ፊደል በ የላይኛዉ ክፍል የሚወክል ነዉ። በስተመጨረሻ የኢኮኖሚዉ እድገት በቀጠለ  ወቅት የገቢ አለመመጣጠን እየቀነሰ ይሄድና በስተመጨረሻ የዜጎች ገቢ ወደ መመጣጠን ያዘነብላል። ይሄ ሁሉ ሂደት የሰላሳ እና ከዛ አመታት በላይ  ሊፈጅ ይችላል። ኢትዮጵያ እየሄደችዉ ያለችዉ የዚህ ሂደት የሚያመላክት ነዉ።

በተመሳሳይ ሁኔታ የሙስና እድገት በኢትዮጵያ እንደ የገቢ አለመመጣጠን ያለዉ መላምት ተመሳሳይ ትንቢት ነዉ ያለዉ። የኢትዩጵያ ኢኮኖሚ እያደገ ያለበት በመጀመርያ ወቅቶች ላይ ነዉ የምንገኘዉ። አስፈሪ የሙስና ምልክቶች እየታዩ ይገኛሉ። የኢኮኖሚ እድገት ሙስና እንዲስፋፋ ራሱን የቻለ ምክንያት (Contributing factor) ነዉ። የኢኮኖሚዉ እድገት እስካለ ደግሞ ሙስና እየጨመረ ነዉ የሚሄደዉ። አሁን የሚታየዉ የሙስና መስፋፋት ምልክቶች የዚህ ተፈጥራዊ ሂደት ዉጤት ነዉ። ስለሆነም የኢትዮጵያ የሃያ አመት እድሜ እድገት ሲኖረዉ ሙስና ሲሄድበት የነበረዉ ፍጥነት በመቀነስ ወደ ኮንስታንት እንቅስቃሴ ይቀየራል። ከዛ ከሃያ አመት ብኃላ የሙስና የመስፋፋት ፍጥነት በስተመጨረሻ እየቀነሰ ይመጣል። የመንግስት ሌቦች በዚህ ስፋት እና መጠን በሕግ ቁጥጥር  ስለ ማዋሉ ትክክለኛዉ

ግዜ (right timing )ነዉ፡፡ ምክንያቱም ኢትዮጵያ እድገት የአስር አመት እድሜ ስላደረገ፡፡ ቀጣዮቹ አስር አመታት ደግሞ ፈጣን እድገት እና የሙስናዉ አስፈሪ ገፅታዉ ገዝፎ የሚወጣበት ጊዜ ስለ ሚሆን፡፡

**<u>ማጠቃለያ</u>**

መንግስት ሙስና ለመዋጋት እየወሰደዉ ያለዉ እርምጃ የሚያስመሰግነዉ ቢሆንም ፤ ትልቁ ትንቅንቅ የሚያስፈልገዉ ሙስና ለቡዙ ዘመናት እንደ ባህል አድርጎ የሞጓዝ ሁኔታ መቀየር ነዉ፡፡ ምክንያቱም የሙስና ምንጬ ማድረቅ እንጂ የመንግስት ሌቦች በመያዝ ሙስና ማስወገድ መይም መቀነስ ከቶ አይቻልም፡፡ የፀረ ሙስና የጦር አዉድማዉ ያለዉ በሰዎች ጭንቅላት እንጂ በመንግስት ሌቦች ቤት ወይም ብር ላይ በመዝመት አይደለም፡፡ በመንግስት ሌቦች ቤት ወይም ብር ላይ በመዝመት የመፍትሄዉ ኢሚንት አካል ነዉ፡፡ የመቅደሱ መሰረት እንዲጠነክር እና የመቅደሱ ምሰሶዎች በፀና መሰረት እንዲቆሙ እንዲሁም የመቅደስ ሲስተሙ እንዲሰራ ሙስናን የሚፀየፍ ሕብረተሰብ እንዲኖረን ተግቶ መስራት ይጠይቃል፡፡

እድገቷ ጨምሮ ሙስና ቀንሶ የምትኖረዉ ኢትዮጵያ ፈጣሪ ያሳየን! አሜን!